# ትዝብት ቁጥር 15

ጥር-24ቀን-2004ዓ.ም(01-02-2012)

## ውሸት እስከ መቃብር

ሰሞኑን በሰፊው ሲነገርና ሲተችበት የከረመው ወሬ በአረመኔው መንግሥቱ ሃ/ማርያም ተጽፎ ለገበያ በቀረበው መጽሃፍ ላይ ነበር።መንግስቱ ሀ/ማርያም ከጻፈው ውስጥ ጠቃሚ ትምህርትና ተመክሮ ይገኝበታል ብዬ ባልገምትም ለመተቸትና ለመታዘብ ስል እኔም መጽሃፉን እንደሌሎቹ ሳነበው የሠራው ግፍና በደል ከፊቴ ላይ ድቅን እያለብኝና እየዘገነነኝ አንብቤዋለሁ።በአጠቃላይ ጽሁፉ የውሸት መደብል ስለሆነብኝ ጸሃፊው "ትግላችን" ብሎ የሰየመውን መጽሃፍ "ውሸታችን" ቢለው የሚስማማው መስሎ ታይቶኛል ።ሰው እያረጀ ሲሄድ ሌላው ቢቀር አንድ እግሩ ከመቃብር ጉድጓድ ውስጥ ሊገባ ጫፍ ላይ መንጠልጠሉን ሲረዳ ከአሁን በኋላ ለምኔ ብሎ እውነቱን ለመናገር የሚቆርጥበት ወይም በአማኞች አባባል ንስሃ የሚገባበት ወቅት ነው።ጉደኛው መንግሥቱ ግን በቁሜ ለብሼ የኖርኩትን የውሸት ካባ የሚገፈኝ የለም፣እኔም አላወልቅም እስከመቃብር ድረስ አንግቤው እዘልቃለሁ ከሞትኩም በኋላ በቋሚነት እንዲኖር በማለት የቀረጠ ይመስላል በመጽሃፍ መልክ የውሸት መዝገቡን ይዞ ብቅ አለ።በዚህ የውሸት ጥራዝ ውስጥ የኢትዮጵያም ያለፈ ታሪክ ተዘግቧል።መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ እንዲባል የታሪክ አዋቂዎችን ሥራ ቦጨቅ ቦጨቅ አድርጎ እራሱን ከታሪክ ጸሃፊዎች ተርታ ለማስቀመጥ የሞከረ ቢመስልም መንግሥቱ የሚታወቅበት ዋናው ገጹና ጸባዩ ታሪክ ጸሃፊነቱ ሳይሆን በገዳይነቱ፣በጸረ ምሁርነቱ፣በራስ ወዳድነቱ፣ በፈሪነቱ ፍርሃቱም በወለደው ጨካኝነቱ ነው።ከዚህ አረመኔ የተገኘው ነገር ቢኖር የሰው ልጅ በተለይም ኢትዮጵያውያን በውስጣችን ተደብቆ የኖረውን ጨካኝነት በይፋ ወጥቶ እንድናየው ማድረጉ ነው።አዎ!ሕዝብ መሪውን ይመስላል ይባል የለ!የዚህ አረመኔ ጽሁፍ ለገበያ መውጣቱ ብቻ ሳይሆን የሚያስገርመው ለመግዛት የሚጠየቀው ገንዘብ ነው።በታወቁ ሊቃውንትና ተመራማሪዎች በጥናት የተደገፈ ትምህርታዊና ጠቃሚ መጽሃፍ በገበያ ላይ ሲወጣ ያልተጠየቀበት ዋጋ በዚህ ወራዳ ሰው የተጫጫረ የውሸት መዝገብ በአውሮፓ 40 ኤሮ ተጠይቆበታል፣ ይህ በኢትዮጵያ ብር ሲሰላ ከ900-1000ብር መሆኑ ነው።በዚህ ሁሉም ነገር ጥንቡን በጣለበት፣በረከሰበት ሰዓት!በሻጭና በደላላነት የተሰማሩት ህሊና ቢስ ግለሰቦች ሌላው ቢቀር ለመሸጥ ዋጋ ከመተመናቸው በፊት መጽሃፉን ከዳር እስከዳር አንብበው የህሊና ፍርድ ሰጥተው ዋጋውን ቢተምኑ የተሻለ ነበር።ግን ያንን ያደረጉ አይመስለኝም ።በሃሳባቸው ለጸሃፊው ካላቸው አምልኮና ፍቅር የተነሱ ይመስላል የመጽሃፉን ዋጋ ከሚገባው በላይ ሰቅለውት ቁጭ አሉ። በመጽሃፍ ገበያ ውስጥ ወይም ስለመጽሃፍ ጥልቅ እውቀት ያላቸው አለመሆናቸውን በቀላሉ ለመረዳት ሲቻል ሌላው ቢቀር ጸሃፊው ማን ነው?በህብረተሰቡ ያለው ተቀባይነት ምን ይመስላል? በመጸሃፉ ውስጥ ምን የሚጠቅምና ትምህርት የሚሰጥ መልዕክት አለው ?ብሎ መመርመር መጽሃፉን ከህትመት ጀምሮ እስከመሸጥ ድረስ የሚደረገውን ተሳትፎ ሊጠቁማቸው በቻለ ነበር።ግን ምንም ይሁን ምንም ፣ማንም

ይጻፈው ማንም፤ጠቃሚ ይሁን ጎጂ፣ተሸጦ ገንዘብ እስካስገባ ድረስ በሚል ፍቅረ ንዋይ አቋም አላፊነትን በመዘንጋት ከመንግሥቱ ጋር በጥቅም ተቆራኝተው ሲሯሯጡ ማየት እራሱን የቻለ ወራዳና ምን ያህል ለገንዘብ ሟች እንደሆኑ የሚያሳይ ድራማ ነው።ነገ ደግሞ ዛሬ የሚያወግዙትና የሚኮንኑት መለስ ዜናዊ መጽሃፍ ጻፍኩ ብሎ ብቅ ቢል ለመሸጥና ለመደለል ይሯሯጡ ይሆናል።ይህን ከሚያደርጉት መሃል በተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈናል፣ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን እንታገላለን የሚሉ ግለሰቦች ናቸው።ለነሱ አንዱና ዋናው ትግላቸው በዚህም በዚያም ብሎ ገንዘብ መሰብሰብ ነው።እንኳን መጽሃፍ ሌላም ቢሆን ከመሸጥና ከመለወጥ አይታቀቡም። በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አገሮች እንደመንግሥቱ ያሉ በሕዝብ ላይ በደልና ግፍ የፈጸሙ ሰዎች እንኳንስ የጻፉት መጽሃፍ በመደብር መደርደሪያ ላይ ሊቀመጥና በአደባባይ ወጥተው ሃሳባቸውን እንዳይገልጡ መደረጉን የጎለበተ የዲሞክራሲ መብት ባለበት በአውሮፓ ለማየት ችለናል።የመንግሥቱ ሃ/ማርያም አይነቶቹ ወንጀለኞች እየታደኑ ለፍርድ በሚቀርቡበት ጊዜ የእኛ ዝም ማለት የልብ ልብ የሰጠው ይመስላል ዛሬ በመጽሃፍ ነገ ደግሞ ማን ያውቃል የፓርቲ ፕሮግራም ነድፎ ተቀበሉኝ ብሎ ይመጣ ይሆናል።ይህ አንድ ቁጥር ነብሰ ገዳይ እስከአሁን ድረስ ከሕግ እርቆ መገኘቱ ለእውነትና ለፍትህ የቆሙ ሰዎች በተለይም ኢትዮጵያዊ የሕግ ባለሙያዎች መከታተልና ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ማድረግ በተገባቸው ነበር።አሁን ግን የተገላቢጦሽ ሆኖ አንዳንድ ሕግ እናውቃለን የሚሉ ሰዎች አንቀጽ እየጠቀሱ በዚህ አረመኔ ሰው የተጻፈውንና የታተመውን መጽሃፍ እንዳይሸጥ በቅድሚያ ኮፒውን አሰራጭተዋል በሚሏቸው ሰዎች ላይ ሕጋዊ ቅጣትና እርምጃ እንዲወሰድባቸው አምርረው በመጠየቅ ላይ ናቸው።

በሌላው አቅጣጫ ደግሞ መጽሃፉን ከህትመት እስከ መሸጥ ድረስ  የተባበሩት አንድም መንግሥቱ ሃ/ማርያምን የሚደግፉና የሠራውን በደልና ግፍ የሚያደንቁ የሥራው ተካፋዮች አለያም በዛም በዚህም እያሉ ገንዘብ ለመሰብሰብ ለጥቅም ያደሩ ይሉኝታ ቢስ ነጋዴዎችና ደላሎች ናቸው።

እዚህ ላይ አንድ ግልጽ ማድረግ የምፈልገው ነገር ቢኖር መንግሥቱም ሆነ ሌላው የሚጽፈው መጽሃፍ አይነበብ አልልም።መነበብ አለበት።ካልተነበበ የሰውየው ውሸትና ማንነት ሊታወቅ አይችልም።ጥሩም ሆነ መጥፎ የሚታወቀው ተነቦ ሲመረመርና ሲጠና ነው።ስላነበብኩትም ነው የመንግሥቱን ውሸት በጥቂቱም ቢሆን ለመግለጽና ለማሳየት የቻልኩት።የምቃወመው ግን መነበቡን ሳይሆን እንደ ትልቅ ጠቃሚ መጽሃፍ አንባቢውን ለመዝረፍ የተጠየቀበት ዋጋ አግባብ ያለው አለመሆኑን ነው።የመጽሃፉም አታሚ የገጠመውን ችግር ሳልረዳው አልቀረሁም።የጉልበቱ ሳይታሰብ መጽሃፉን ለማተም ለወረቀትና ቀለም ወጭ አድርጓል።ሆኖም ግን አሳታሚው አስቀድሞ ጸሃፊው በኢትዮጵያኑ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና አመኔታ መመርመር ነበረበት።በጽሁፍ ነጻነት ሽፋን አሰሱን ገሰሱን አትሜ እጠቀማለሁ ብሎ ያደረገው ከሆነ ለኪሳራው እርሱ ራሱ ተጠያቂ ነው እንጂ አልገዛም ያለው ወይም በሌላ መንገድ በመዋስም ሆነ በስጦታ ያገኘው አንባቢ አይደለም።ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ዘላለም ሲያለቅስ ይኖራል ነውና የመጽሃፉ አታሚ የደረሰባቸው ጉዳት በራሳቸው ምርጫና ውሳኔ ከመንግሥቱ ሃ/ማርያም ጋር በፈጸሙት ውል የተከሰተ ይመስለኛል። የአሁኑን ጥፋታቸውን "አይውሉ ውሎ

ውዬ ከመንግሥቱ ሃ/ማርያም ጋር ተዋውዬ፣የጻፈውን መጽሐፍ አትሜ ለመሸጥ ብወጣ ኮፒው ተሰራጭቶ አገኘሁት" እያሉ ለወደፊቱ እንዲህ ካለው አክሳሪ ተግባር እሳቸውም ሆኑ ሌሎቹ እንዳይነከሩ ትምህርት ያገኛሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።ለአሁኑ ለደረሰባቸው ኪሳራ ግን እንደመንግሥቱ ሃ/ማርያም ሥራና እንደሳቸውም ግዴለሽነት ሳይሆን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ለቀለምና ለወረቀት ላወጡት ወጭ መጽሃፉን ያነበበ ሁሉ የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርግ በዚህ አጋጣሚ እጠይቃለሁ።እኔ በበኩሌ ከዚህ በፊት አታሚው ከሚኖሩበት አገር 500 ገጽ ያለው መጽሃፍ በሽያጭ ወቅት አምስት ዶላር ስለገዛሁ ያንኑ ያህል ገንዘብ ልልካላቸው ዝግጁ ነኝ።ምክንያቱም በቀለምም በገጹም ብዛት ተመሳሳይ ስለሆነ ተመሳሳይ ዋጋ መክፈሉ ተገቢ ነው በማለት ነው።በአለሁበት አገርም በአሁኑ ጊዜ ባለው የኤኮኖሚ ድቀት ታዋቂና ተወዳጅ ጸሃፊዎች የጻፉት መጽሃፍ ከዚህ በላይ አይጠየቅባቸውም።ለዛውም መንግሥቱ ለጻፈው የውሸት ጥራዝ መጽሃፍ ሳይሆን የአታሚውን ድካም በማየት ሃዘን ስለተሰማኝ ነው።ሆኖም ግን ከአታሚውም በኩል የምጠይቀው የአታሚ መብቴን ተጋፍተውና ካለፈቃዴ ኮፒውን አሰራጭተው ገቢዬን አከላከሉኝ በማለት ሊመሠርቱ የሚያስቡትን ክስ ማንሳት ይኖርባቸዋል።እንዲያውቁት ያህል ማንም ሰው ካለአታሚውና ያለጸሃፊው ፈቃድ 85% የሚሆነውን የመጽሃፍ ይዘት ሊያትምም ሆነ ሊያሰራጭ እንደሚችል ነው።ለጠበቃ የሚያወጡት ገንዘብ እራሱ ተጨማሪ ኪሳራ እንደሚሆንባቸው ሊገነዘቡት ይገባል።በኮፒው ማሰራጨትም የሚጠረጠሩት ደጋፊዎች እንዳላቸውና ለጠበቃ የሚሆን ገንዘብ እንደማይነፍጓቸው ማወቅ ጥሩ ነው።በሁለቱም በኩል ተጠቃሚው ነገር እያጦዘ በፍርድ ቤት ለመቆም የሚጥረው ጠበቃ ነው።ስለሆነም በሁለቱም በኩል የተሠራው ለወደፊቱ ትምህርት ሆኖ ጉዳዩ በዚሁ ላይ ቢቆም የተሻለ ነው።

ሌላው ጉዳይ መጽሃፉ በሽያጭ ሳይሆን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ተሰራጭቷልና አሰራጭው በሕግ መጠየቅ አለበት ብለው አንቀጽ እየጠቀሱ የሚከራከሩ ጠበቆች እንዳሉ ለመረዳት ችያለሁ።የአታሚውን ጥቅም በማስጠበቅ ስም እንዲህ የምትሉት ሰዎች በፍትህ የምታምኑና ለሕግ መከበርም የቆማችሁ ከሆነ የመንግሥቱ መጽሐፍ ካለገንዘብ ተሰራጨ ብላችሁ ያሰራጩትንም ለመክሰስ ከማቆብቆባችሁ  በፊት መንግሥቱ ሕዝብ የጨረሰ፣አገሪቱን ካለመሪ አስቀርቶ፣ጦሩን አጋፍጦ፣አገሪቱን ለወያኔ አስረክቦ የጠፋ ከሃዲ መሪ፣ስለሆነ እንደ ቀሩት አምባ ገነኖች በዓለም ፍርድ ቤት ቀርቦ ቅጣቱን ይቀበል ብላችሁ ጠይቃችኋል?ወይስ አፍንጫን ሲመቱት ዓይን ያለቅሳል ሆኖባችሁ ነው እስከ ዛሬ በመንግሥቱ ሃ/ማርያም ላይ ያልገለጣችሁት ወንጀለኛ መቅጫ አሁን ትዝ ያላችሁ።

ወደ ዋናው እርዕሴ ልመለስና በ"ውሸት እስከመቃብር "ላይ ትንሽ አስተያየት ልስጥ፤

ከሁሉ መጀመሪያ መጽሃፉን ከመተቸቴ በፊት መጽሃፉን በጻፈው ግለሰብ ላይ ያለኝን ቀጥተኛ እውቀትና ተመክሮ ለማሳየት እሞክራለሁ።

መንግሥቱ ሃ/ማርያምን በአካል ሁለት ጊዜ አገኝቸዋለሁ።የመጀመሪያው ሰኔ 30 ቀን 1966 ዓ.ም.የዛሬ 38 ዓመት ከእሥር ቤት ከሌሎቹ ጓደኞቼ ጋር ተፈትቼ በደርግ ጽ/ቤት አዳራሽ ውስጥ በተገኘሁበት ጊዜ ነው።ይህንን በመጽሃፉም ውስጥ በገጽ 158 በምዕራፍ አምስት ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡...."በልጅ እንዳልካቸው የታሰሩት መለዮ

ለባሹን በአመጽ የቀሰቀሱና የገፋፉ ናቸው ተብለው በመወንጀል የታሰሩትን ግለሰቦች በመፍታት የመንፈስ ተሃድሶ አድርገንላቸው ወደነበሩበት ሥራቸው መመለስ ነበር......ቅድሚያውን የሰጠነው በምድር ጦር ወታደር ፓሊስ በሚጠበቀው እስር ቤት ለታሰሩት ለአየር ሃይል አባላት ነበር።ለጓዶቼ ክብርና የሞራል ተሃድሶ ስንል ነጻ መለቀቃቸውን ያሳወቅናቸው የደርጉ ጉባኤ አዳራሽ ጠርተን ነበር።"አዎ በዚያን ወቅት ነው እኔና የቀረነው 21 ሰዎች እንደ ጸሃፊው አገላለጽ የአየር ሃይል ባልደረቦች ብቻ ሳንሆን የክብር ዘበኛ፣የአራተኛ ክ/ጦር፣የአየር ሃይል፣የአርሚ አቪየሽን፣የአየር ወለድ፣ከአዲስ አበባ ከደብረዘይትና ከአስመራ የአድማ መሪዎች ተብለን ተለቅመን የታሰርን ሰዎች በተለቀቅንበት ሰዓት መንግሥቱን ያየሁት።በዚያን ጊዜ ዕድሜው ከ35 ዓመት ያላነሰ፣ ቁመቱ ከ1.70 ቢያንስ እንጂ የማይበልጥ፣ክብደቱም ከሰውነቱ አንጻር ከ70 ኪሎ የማያልፍ(ምናልባት አጥንተ ከባድ ሆኖ ካላለፈ በስተቀር)ከንፈሩ ደንዳና፣ፊቱ ጥቁርና ሻካራ፣ጸጉሩ አጭርና ከርዳዳ፣ቅጠልያ የወታደር ዩኒፎርም የለበሰ ፣የሱሪው ግርጌ በላስቲክ ተሰብስቦ ከረጅም/ቦት/ጫማ በላይ የወደቀ ነበር።በዚያን ጊዜ ውጫዊ ገጹን እንጂ ውስጣዊ ገጹን ለማወቅ አልቻልኩም።

ለሁለተኛ ጊዜ ያየሁት በመስከረም ወር 1967 ዓ.ም.ደርግ እራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ብሎ ሥልጣን ሲይዝ በመቃወምና ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፣አገር ለመምራት ያልመረጥነው የወታደር መንጋ ወደየመጣበት ክፍል ይመለስ የሚል አቋም ይዘን በተቃዋሚ ጎራ በመሰለፋችን፣ይህንንም የሚገልጽ ለውጥ ማለት በሚል እርዕስ አስራ አንድ ነጥቦችን የያዘ ጽሁፍ በሄሊኮፕተር በአዲስ አበባ ውስጥ፣በመርጨታችን እንዲሁም የአርሚ አቪየሽን አዛዥ የነበሩት ኮሎኔል ይገዙ ይመኑ ከእኛው ጋር በማበራቸውና ለደርግ ታማኝነታቸውን እንዲገልጹ ተጠይቀው ለሕዝባዊ መንግሥት እንጂ ሕዝብ ላልመረጠው ቡድን ታማኝነቴን አልገልጽም በማለታቸው ታፍነው በመታሠራቸው እንዲለቀቁ በማለት ላቀረብነው ጥያቄና በዚያም የተነሳውን ውዝግብና ልዩነት ለማብረድ የደርጉ ሊቀመንበርና ርዕሰብሔር ሆነው የተሾሙት ሌ/ጀነራል አማን አምዶም በቢሮቸው ጠርተውን ባነጋገሩን ወቅት ነበር።ከደርግ በኩል በጀነራሉ ቢሮ ተጠርተው የመጡት ስድስት ሰዎች ሲሆኑ እነሱም መንግሥቱ፣ደበላ፣ሲሳይ፣ተስፋዬና፣ ፍቅረሥላሴ ሲሆኑ ከአርሚ አቪየሽን ደግሞ በላይ ጸጋዬ ፣ተስፋዬ ተክሌ፣ዩሃንስ ወ/ጊዮርጊስ፣ዩሃንስ ወርቅነህና እኔ ነበርን።በዛ ጊዜ መንግስቱ ቀድሞ ከነበረው የአለባበስና የአቀራረብ ልዩነት ባይበትም ያው መንግስቱ ነበር። አለባበሱ የካኪ ሳርያን ሞድ፣ጉርድ ጥቁር ጫማ፣ፊቱም በቅባት ይሁን በድሎት ካለፈው ጊዜ ካየሁት ወዛ ብሎ ነበር የቀረበው።የተፈጠረውን ለመዘርዘር ጊዜውና ቦታው ስለማይፈቅድልኝ ወደፊት በሰፊው ለማቅረብ ሃሳብ አለኝ።ስብሰባችን በጀነራሉ ቁጣና ዛቻ ተውጦ ለጥያቄያችን አጥጋቢ መልስ ሳናገኝ ከ45 ደቂቃ በኋላ ቢሮአቸውን ለቀን ወጣን።

ከጊዜ በኋላ ግን ከማውቀው የሰውነት ቅርጹ ጎላ ብሎ የታየኝ፣ ውስጣዊው መልኩ፣እራስ ወዳድነቱ፣ ፈሪነቱ ፍርሃቱ የወለደው ጭካኔውና ውሸታምነቱ ነው።ውሸቱን በጻፈው መጽሃፍ ሳይደብቅ ገልጾታል።ከውሸቱ መካከል ለምልክት ያህል ከዚሁ መጽሃፍ ውስጥ እየጠቃቀስኩ ላሳያችሁ።

ከደርግ መቋቋም በፊት በወታደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ መሪ ሚና እንደተጫወተና ለደርግም መመሥረት በህቡዕ ይሯሯጥ እንደነበረ በገጽ 128-130 እንዲህ ሲል

ያቀርባል፡"የጦር ሃይሎች ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት ሦስተኛ ክ/ጦር ከሌሎቹ የጦር ክፍሎች ጋር ባደረገው ውልና ትብብር መሠረት አራተኛ እግረኛ ብርጌድን በመወከል ከሦስተኛ እግረኛ ክ/ጦር ህቡዕ ኮሚቴ ጋር አገናኝ የነበረው ሻለቃ ከተማ አይተንፍሱ፣የምድር ጦር ታንከኛ መምሪያን በመወከል ሻለቃ ተስፋዬ ገ/ኪዳንን የሰሜን ሁለተኛ እግረኛ ክ/ጦር በመወከል ሻለቃ ነሲቡ ታዬና ሦስተኛ ክ/ጦርን በመወከል አዲስ አበባ ተቀምጦ የአዲስ አበባን አካባቢ የጦር ክፍሎችና የኢትዮጵያን አየር ሃይል ከሦስተኛ ክ/ጦር ህቡዕ ኮሚቴ ጋር አገናኝ የነበረው ሻለቃ ተፈራ ተክለአብ ነበሩ። ቀጥሎም ...."በተሰጠኝ የአንድ ሳምንት ፈቃድ የጊዜ ክልል ውስጥ ናዝሬት ያለውን የታንከኛውን መምሪያ፣ደብረዘይት የአየር ሃይሉንና የአየር ወለዱን ጦር ሠፈር፣የምድር ጦር የአየር ክፍሉንና(አርሚ አቪዬሽኑን)የገነት የጦር ት/ቤትን በተለያዩ የሥራ ሰበቦች ከሻለቃ ተፈራ ተክለአብ ጋር ሆነን በመጎብኘት ከብዙ ሰዎች ጋር ተገናኘን" በማለት የሌለ ታሪክ ፈጥሮ ያወራል፡፧ እኔ እስከማውቀውም ሆነ ሌሎቹንም ጠይቄ እስካረጋገጥኩት ድረስ ከየካቲት በፊትም ሆነ በኋላ እስከ ሰኔ 23 ቀን ድረስ መንግሥቱ የሚባል ሰው በወታደሩ ንቅናቄ ውስጥ እንኳን ሊመራና ሊያስተባብር ቀርቶ የጎላም ተሳትፎ አልነበረውም።በጦሩ ሳይሆን በአዛገፉ ተልኮ በመምጣት የተቀላቀለው አስተባባሪ ኮሚቴው በተቋቋመ በሶስተኛው ቀን ነበር።የተቋቋመው በሰኔ 21 ላይ ነው።አጥናፉ አባተ፣ዩሃንስ ፍትዊ፣ግርማ ፍስሃ፣ተፈራ ተክለአብና ብዙአየሁ አምሳሉ ቀኑን ሙሉ ሲማከሩና በየቦታው ሲያስተባብሩ ውለው ማታ በቴሌቪዥን የሚነበበውን ጽሁፍ "ኢትዮጵያችን ትቅደም" በሚል ዕርእስ በብዙአየሁ አምሳሉ የተጻፈውን ግርማ ፍስሃ ለዕለቱ የቴሌቪዥን አንባቢ ተረኛ ለነበረው በመስጠት እንዲነበብ ተደረገ።ይህ ጉደኛ ግን ከራሱ ጭንቅላት ያወጣው መፈክር አድርጎ አቅርቦታል።"ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለው መንፈስ በሰብሳቢዎቹ ና በመጀመሪይ በተሰበሰቡት ዘንድ ይገለጽ ስለነበር የሊቀመንበርነቱን ቦታ ሲይዝ ያንኑ መርሆ በሰሌዳ ላይ ለመጻፍ በቃ።

ስለተፈታነው ሰዎች ሲያትት "እነዚህ እስረኞች ከታሰሩበት ሌላ በተጨማሪ ሁል ጊዜ እንዳስባቸው ወይም እንዳስታውሳቸው ያደረገኝ እስር ላይ በነበሩበት ጊዜ ታጋይነታቸውና አብዮታዊ ወኔያቸው ሳይቀዘቅዝ አርቀው በማሰብ በአብዮቱ ያዘጋጁት ታሪካዊና በኢትዮጵያ ሕዝብ እጅግ ተወዳጅ የሆነውን "ተነሳ ተራመድ የሚለው አብዮታዊ መዝሙራቸው ነበር"ይልና እንደዚህ የሚያደንቀን ሰዎች ደርግ ተወግዶ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ብለን በተነሳንበትና በተቃወምንበት ጊዜ ደግሞ የኻሊት ዞሮ ወይም ተቀልብሶ በገጽ 177 አንቀጽ 5 እንዲህ ሲል ይወነጅለናል"ከመሃሉ መርጦ የላከን ሰራዊት በራሱ ውስጥ ባሉ የአብዮቱ ጸሮች እየተገፋ ያስቸግረን ነበር። በሰሜን የሁለተኛ እግረኛ ክፍለ ጦር፣በአየር ሃይሉ፣በምድር ጦር አየር ክፍል(አርሚ አቪዬሽን)፣ በምድር ጦር መሃንዲስ ክፍል ፣በምድር ጦር ወታደር ፖሊስና የክብር ዘበኛው ክፍል ጦር ውስጥ የነበሩ ጥቂትም ቢሆኑ ፀረ አብዮተኞችና ሥርዓተ አልበኞች ነበሩ"ብሎ ይከሰናል።በክስም ብቻ አላቆመም በፈጸመው ጭፍጨፋ አብዛኛዎቹ የማውቃቸውና አብሬአቸው የነበሩትን ሃቀኛ ታጋዮች በህዳር ወር በከርቸሌ እስር ቤት ከባለሥልጣኖች ጋር ቀላቅሎ እረሸኗቸዋል።በጣም የሚያሳዝነው ነገር ግን እስከአሁን ድረስ ሕዝብ ሳያውቅላቸውና ሳያውቃቸው ከአርሚ አቪዬሽን እንደ ኮሎኔል ይገዙ ይመኑ፣ ሻምበል በላይ ጸጋዬ፣መቶ አለቃ ተስፋዬ ተክሌ፣ጁኤክማን ዩሃንስ ፍትዊና ሌሎቹን የመሰሉ ለዲሞክራሲ ለውጥ ይጮሁና ይታገሉ የነበሩት ችሎታ ያላቸውና ወጣት ዜጎች

ከባለሥልጣኖቹ ጋር በመረሸናቸው የሥልጣን ተካፋይና አገር የበደሉ ተደርገው በሕዝቡ "ስልሳዎቹ ባለሥልጣኖች"እየተባሉ መጠራታቸው ነው።ባለሥልጣኖቹም ቢሆኑ በሕጋዊ መንገድ ተፈርዶባቸው የተረሸኑ ሳይሆን በግፍና በጭፍን የተገደሉ በመሆናቸው አስፈጻሚና ፈጻሚዎቹን በሕግ ያስጠይቃል። የተወሰደው የእብደት እርምጃ ተስፋ ከመቁረጥ የተነሳ እንጂ በሰከነ አእምሮ ታስቦበትና ተመክሮበት የተደረገ ሕጋዊ አሠራርን የተከተለ አይደለም።ጄነራል አማን አምዶም በማስቸገራቸው ሳይጨርሱን እንጨርሳቸው በሚል ወከባ የተፈጸመ ግድያ ነው።የዚህን እርምጃ ጥንስ ሃሳብ የወሰደው ከነጀነራል መንግሥቱ ነዋይ ውድቀት መሆኑን በገጽ 51 አንቀጽ 3 በመስመር 6 ላይ እንዲህ ይለዋል።"...ተቃዋሚዎቹን መሳፍንታዊ ጀነራሎች በቅድሚያ ለቃቅመው ቢያሥሩ ኖሮ ወታደራዊው ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካውም ይዘት ተለውጦ ሌላ ታሪክ በተከሰተ ነበር።" እሱ ግን ለቃቅሞ ማሠር ብቻ ሳይሆን በቁጥጥር ሥር የዋሉትን ሁሉ በጅምላ እረሽኖ በጉድጓድ ውስጥ ኖራ ነስንሶ ቀበራቸው።ይህ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝብን ያስደነገጠ አረመኔአዊና አሰቃቂ ግድያ ነው።ጄነራል አማንን ደግፎ ይወጣል ተብሎ ይፈራ የነበረው ጦር ተደናግጦ በመቅረቱ ለቆሙለት ወታደራዊ አገዛዝ በር ከፈተላቸው።በፍርሃትና በሽብር ለመግዛት መቻላቸውን አበሰረላቸው።

ይህ አረመኔ ሰው ለአስራሰባት ዓመት የፈጸመውን ጭካኔና እራስ ወዳድነት የጀመረው ገና ከጧቱ ነበር።መርጦ ልኮኛል ያለው የሶስተኛ ክፍለ ጦር አትወክለንምና ተመለስ አለበለዚያ በቤተሰቦችህ፣በሚስትህና በልጆችህ ላይ እርምጃ እንወስዳለን ብለው ሲሉት"ብትፈልጉ ቀቅላችሁ ብሏቸው እንጂ አልመለስም"ያለው ምን ያህል እራሱን ወዳድና ጨካኝ እንደሆነ የሚያበስር ምልክት ነበር።በአንዳንዶቹ የተሳሳተ አባባል ግን አገሩን ከምንም በላይ የሚወድ ነው እያሉ ሲመሰክሩለት ይሰማል።አገር መውደድ ትርጉሙ ያልገባቸው በመሆኑ ሊታዘንላቸው ይገባል።አገር መውደድ ማለት ሕዝብ መጨፍጨፍ፣ማሸበር፣ ማሰደድ፣ጦሩን አጋፍጦ ወያኔን ለመሰለ ጸረ ኢትዮጵያ ሃይል አገሩን አሳልፎ መስጠት አይደለም።ብዙ አገራቸውን የሚወዱት ኢትዮጵያውያን መሪዎችና የጦር አበጋዞች በጦር ሜዳ መስዋዕት በመሆን ያለፉ እንጂ ለውጭ ሃይሎች ፍላጎት ተገዝተው አገር ጥለው የኮበለሉ በታሪክ አልበቀሉም።ታሪካችንንም እኛንም ያዋረደ መንግሥቱ ሃ/ማርያምና የሱ አጃቢ የሆኑት ባለሥልጣኖች ናቸው።

በገጽ 43 ላይ እንዲህ ይላል"ኢትዮጵያ ዛሬ ጀግና ብቻ ሳይሆን ሰው አልባ ምድረበዳ እየሆነች ነው።ዛሬ ሰው የምንላቸው ኢትዮጵያውያን አንድም ተገለዋል፣አንድም ተሰደዋል፣አብዛኛው በወያኔ እስር ቤቶች ታጉረዋል።በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚዋጋና የሚታገል ቀርቶ የሚናገርም የለም።ነጻ ያወጡት አብዮታውያን መሪዎችና የአገሪቱ ወጣቶች በወያኔ እስር ቤቶች በረት የተዘጋባቸው መሆናቸውን አያስተዋለ ሁሉም ዝም ብሏል"

ይህች ናት ጨዋታ! በሽ የሚቆጠሩትን ያገሪቱን ዜጎች፣ ወጣቶች፣ምሁራን፣ሠራተኞች በግፍ እንዳልጨፈጨፈ፣የአካል ጉዳተኞች እንዳላደረገ፣በእስራት እንዳላሰቃዬ እንዳላሰደደ የዲሞክራሲው አባት፣የነጻነት ጌታ፣የሕዝብ ድምጽ አክባሪ እንደሆነ ሁሉ በወያኔ የሚፈጸመውን በደል ለመሰንዘር ሲቃጣ እራሱን ያላወቀ እብድ መሆኑን የዘነጋው ይመስላል።በሱ አባባል ኢትዮጵያውያን ማለት እንደሱ በጭካኔ ሕዝብ የቁም

ስቃይ ያሳዩትን አረመኔ የደርግና የኢሰአፓ አባላትን፣ጨካኝ ካድሬዎችንና በአብዩት ጥበቃ ስምያሻቸውን ያደረጉትን የቀበሌ ነፍሰ ገዳዮችን ነው።አምባ ገነንነትን የሚቃወሙ፣ለሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና ለዲሞክራሲ የሚታገሉት ዜጎች ለሱ ሰዎች አይደሉም።ይሉኝን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ነውና ማንነቱን ስለዘነጋው እንዲያውቀው ማድረግ ይገባል።በኔ በኩል ሌላው ቢቀር ካነበብኳቸው መጻህፍት መካከል"ምርኮኛ" በሚል እርዕስ የተጻፈውን መጽሃፍና በራሱ ጓደኛ በሻለቃ ዳዊት ቀደም ሲል በእንግሊዝኛ የተጻፈውን "ቀይ እንባ"(red tears)የሚለውን፣እንደመግደል የማንበብ ፍቅርና ሱስ ካለው እንዲያነበውና እራሱን እንዲያውቅ ምክር እለግሰዋለሁ።

ወደ መጽሀፉ መጀመሪያ ላይ ስለወታደሩ ንቅናቄ ላይ በተለይም ስለራሱ ተሳትፎ የገለጸው በፍጹም ውሸት መሆኑንና ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደሚባለው ሆኖ አገኝቸዋለሁ።መንግሥቱ ሃ/ማርያም የሚባል ወታደር በመጀመሪያዎቹ አምስት ወራት ወታደራዊ ንቅናቄ ውስጥ እንኳንስ ሊያስተባብርና ሊመራ ቀርቶ የሚታወቅም ተሳትፎ አልነበረውም።ይህንንም በራሱ አባባል  በገጽ 58 ላይ የአብዮቱ ዋዜማ በሚለው እርዕስ ሥር  ሲያስቀምጠው"...ከጥር አራት ቀን 1966 እስከ የካቲት 21 ቀን 1966 ዓ.ም.ድረስ ሠራዊት ሳይመርጣቸው በመጠራራት እራሳቸውን መርጠው በአራተኛ እግረኛ ክ/ጦር ግቢ በመሰባሰብ የጦር ሃይሉን አንደኛውን ዙር ንቅናቄ የመሩት በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ያሉ ከፍተኛ መኮንኖች የአቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድን መንግሥት አፍርሰው የልጅ እንዳልካቸው መኮንን መንግሥት እስከአቋቋሙበት ያለው የጊዜ ክልል ነው"እዚህ ላይ በአራተኛ ክ/ጦር ከፍተኛ መኮንኖች ተሰብስበው ንቅናቄውን መሩ ያለው ውሸት ከመሆኑም በላይ እሱ ለእንቅስቃሴው ባዳና እንግዳ መሆኑን ታሪኩን አዛብቶ ማቅረቡ ያረጋግጣል።በየካቲቱ ወታደራዊ እንቅስቃሴ የተሳተፉት ሙሉ ለሙሉ የበታች ሹማምንቶችና ተራ ወታደሮች ነበሩ።ከነገሌ ወደ አሥመራ፣ደብረዘይትና አዲስ አበባ የተዛመተውን እንቅስቃሴ የመሩት እነዚሁ በኑሮ የተጎዱት የሠራዊቱ አባላት ነበሩ እንጂ አንድም መኮንን አልነበረም።በኑሮና በትምህርት ደረጃቸው ይሻሉ የነበሩት የአየር ሃይልና የአርሚ አቪዬሽን ባልደረቦች ግን በማስተባበር ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።የአዲስ አበባውን እንቅስቃሴ የመሩት የአርሚ አቪየሽን ባልደረቦች ሲሆኑ የዕዝና የስርጭት ጣቢያውም አሮጌው አየር ማረፊያ ተብሎ ይጠራ በነበረው በአርሚ አቪየሽን ግቢ ውስጥ ነበር።

እራሱን የትግሉ ተካፋይ ለማድረግ ሲል ደርግን ለማቋቋም ምክንያትና የመጀመሪያ የመሠረት ድንጋይ ካስቀመጡት ጥቂት ሰዎች ጋር እራሱን ለማቀላቀል ሞክሯል። ውስጥ ውስጡን በሚስጥር እየተገናኙ ወታደሩን ለማስነሳትና እኛንም ለማስፈታት አመቺ ጊዜ ይጠብቁ ከነበሩት መካከል አንዱ ከነበረው ከሻለቃ ተፈራ ተ/አብ ጋር አዲስ አበባ ድረስ  እየመጣሁ በሚስጥር እየተገናኘሁ ስለወደፊቱ ትግል እየተማከርኩ እሄድ ነበር።በዚህም ጉዞዬ ከጀኔራል አማን ጋር በተፈራ በኩል ተገናኝቼ ተወያይቻለሁ ሲል አትቷል።እራሱን ሻለቃ ተፈራን እንዲቀላቀላቸው ያደረጉት በሚስጥር የሚገናኙት ዩሃንስ ፍትዊ፣ብዙአየሁ አምሳሉ፣ግርማ ፍስሃና ሻለቃ አጥናፉ አባተ ናቸው።የሃረሩን ጦር ለማሳደም እንዲረዳቸው ከክፍለ ጦሩ ተልኮ አዲስ አበባ መሃንዲስ ኮሌጅ ውስጥ የሚማረውን ሻለቃ ተፈራን ሻለቃ አጥናፉ ስለሚያውቀው በመቅረብ በሃሳባቸው ስለተስማማ ደርግ ሲመሠረት አብሯቸው ነበር።በኋላ ግን በሱና በመንግሥቱ መካከል

በተፈጠረው የውክልና ጭቅጭቅ የተነሳ ከደርግ ተወግዶ በጥበቃ ሥር ዋለ።ከጀነራል አማን ጋርም ለመገናኘት የበቃው የደርግ አባላት ወታደሩን የሚያስተባብር አንድ አንጋፋ ና የታወቀ የጦር መኮንን በመሪነት ይቀመጥ ብለው በወሰኑት መሠረት በሰኔው ወር መጨረሻ እንጂ እሱ እንደሚለው በሱ ምክንያትና ፍላጎት እንዲሁም ቀድሞ በነበረው ምስጢራዊ የትግል ውይይት የተነሳ በመሳሳብ የተሾሙ አይደለም።

በመጀመሪያው ሰዓት ደርግ እንደደርግ ሳይሆን ጦሩን ከሰበሰቡትና ከመሩት አምስቱ መካከል ሦስቱ የአርሚ አቪየሽን ባልደረቦች ነበሩ።ብዙአየሁና ዩሃንስ ፈትዊ የአስተዳደር ክፍል ሠራተኞች ስለነበሩ ሥራው በመስታጎሉ ምክንያት አንዳቸው ወደ ክፍላቸው እንዲመለሱ ስለተወሰነ ብዙአየሁ ወደ ጦር ክፍሉ ወደ አቪየሽን ተመልሶ በንዑስ ኮሚቴው ውስጥ ተቀላቀለ።ከየክፍሉ ሁለት ሰው ይምጣ በተባለ ጊዜ ግርማ ፍስሃና ዩሃንስ ፍትዊ እንዳሉ ሆነው ሌሎች ተጨማሪ ሰዎች ክፍላችንን ወክለው ተቀላቀሉ፣እነሱም ሻምበል ገናናው መንግሥቱ(በኋላ ብርጋዴር ጀነራል ማዕረግ ደርሶ በ1983 ዓ.ም.መፈንቅለ መንግሥት ከሌሎቹ ጋር ተጠርጥሮ ተገሏል)ሲኤክማን ለገሰ ገ/ሥላሴ ነበሩ።አሁንም የአቪየሽኖቹ ተወካዮች በዝተዋል ተባለና ግርማ ፍስሃና ዩሃንስ ፍትዊ ቀርተው ሌሎቹ ተመለሱ።በኋላ ግርማ በጤና ምክንያት ለህክምና ወደ ውጭ አገር ሲሄድ እሱን እንዲተካ መቶ አለቃ ተስፋዬ ተክሌ ተመርጦ ተላከ።በመጀመሪያው ላይ ከጠነሰሱት ሰዎች መካከል በህይወት የሚገኘው አንድ ብቻ ነው እሱም ግርማ ፍስሃ ነው።ዩሃንስ ፍትዊ፣አጥናፉ አባተ፣በዚሁ አረመኔ እጅ ሲገደሉ፣ብዙአየሁ አምሳሉ ሰባት ዓመት ከታሰረ በኋላ ተፈቶ በዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ የሶስተኛ ዓመት ትምህርቱን ሲከታተል እንደሱው ሰባት ዓመት ታሥሮ ተለቆ በሥራ ላይ የተሰማራው በየካቲቱ የመጀመሪያው ንቅናቄ ወቅት የአየር ሃይሉን የመራው ማስተር ግርማ ዘለቀ እንደገና ልትታሠሩ ነው የሚል ወሬ በመስማታቸው ለማምለጥ በጎጃም በኩል ለመውጣት ሲሞክሩ ብቸና በተባለው ወረዳ በገበሬ ማህበር በመከበባቸው እጃቸውን ከመስጠት ይልቅ እራሳቸውን ለማጥፋት በመወሰናቸው በያዙት ሽጉጥ ህይወታቸውን አጥፈተዋል።ተፈራ ተ/አብ ከሰባት ዓመት በላይ ታስሮ ከተፈታና ትንሽ ከቆየ በኋላ በህመም አርፏል፣ግርማ ፍስሃ ደርግ በተቋቋመ በሳምንቱ የመኪና አደጋ ደርሶበት ለአስቸኳይ ህክምና ወደ ጀርመን ወጥቶ እስከአሁን ድረስ በዚሁ አገር ውስጥ ይኖራል።ይህን የዘረዘርኩት መንግሥቱ ሃ/ማርያም ለማንም የማይራራና ይሉኝታ የማይሰማው መሆኑንና ከሱ ይበልጥ ለለውጡ የጣሩትን ግንባር ቀደም ታጋዮች ማጥፋቱን ለማሳየት ነው።

በተማሪውና በምሁሩም ላይ የሚያወርደው ውርጅብኝ አይጣል ነው።ትርጉሙን ቀርቶ ቃሉን የማያውቀውን አብዮት የሚሉ ነገር እንዲያውቀውና የሶሻሊስትን ጽንሰ ሃሳብ ናላውን እስኪያዞረው፣እንደጠበል የጋቱትን፣የመሬት ላራሹን መፈክር አስተጋብተው እንዲያስተጋባ የረዱትን የትግሉ ሻማ አቀጣጣይ የሆኑትን ተማሪዎች፣ምሁሮች በገጽ 55 በሁለተኛው አንቀጽ በ3ኛው መሥመር ላይ እንዲህ ሲል ይከሳቸዋል"ለኢትዮጵያ ሕዝብ መፍትሔ ፈላጊ ከመሆን ፈንታ የነባሩ ችግር አካልና በተጨማሪም ለአገሪቱ አዲስ ችግር ፈጣሪ ወደ አደረጋቸው ሁኔታ አመሩ" ይላል።የሱን ሥልጣን በሚቃወሙበት፣ ለሕዝባዊ መንግሥት መቋቋም በሚጠይቁበትና በሚታገሉበት ጊዜ ችግር ፈጣሪዎች ፣የቀድሞው ሥርዓት ደጋፊዎች፣አናርኪስቶች(ሥርዓት አልበኞች)

ወዘተ እያለ ለመኮነን ተነሳ።አዎ ሁሉም አምባገነኖች ተቃዋሚዎቻቸውን እንዲሁ የማይሉትና የማያወጡለት ሥም የለም።የሱ ቢጤ ጋዳፊም ተቃዋሚውን ያገሩን ሕዝብ እንዲሁ አይጦች፣አሸባሪዎች እያለ ነው እንደ አይጥ ከጉድጓድ አውጥተው በሚዘገንን መልክ እስከገደሉት ድረስ ይጮህ የነበረው።አሁንም ወያኔ ዲሞክራሲ ሥርዓት ይስፈን፣ዘረኝነት ይቁም፣የአገር ዳር ድንበርና የሕዝቦች አንድነት ይጠበቅ፣ሰብዓዊ መብት ይከበር የሚሉትን ነው ሽብርተኞች፣ነፍጠኞች…ወዘተ እያለ በመወንጀል የሚገለውና የሚያስረው።አምባ ገነኖች አንድ የጋራ መለያ ቢኖራቸው ይኸው ጸረ ሕዝብ መሆናቸውና ከራሳቸው በላይ አርቀው አለማሰባቸው ነው።

ወደሌላው ስለ "ቤተ እስራኤል" ወይም "ፈላሻ" ስለተባሉት ወገኖቻችን በገጽ 16 ላይ በሰባተኛው አንቀጽ በአራተኛው መስመር ላይ ጀምሮ ያሰፈረውን ውሸት እንመልከት፤"….ሆኖም ፈላሾች (አይሁዶች)ናችሁ ተብለው ወይም እነሱው እራሳቸው አምነውበትና ነን ብለው ከአገራቸው ከኢትዮጵያ በየጊዜው ወደ እስራኤል ሃገር ዳግም ሲሰደዱ ይታያሉ።በእርግጥ ፈላሾች የሚሸሹት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነው ወይስ ድህነትን?መልሱን ለነሱ እተዋለሁ"ይላል

እርግጥ ነው የቤተ እስራኤል ወይም ፈላሻ ተብለው የሚታወቁት ወገኖቻችን ኢትዮጵያዊነታቸውን ጠልተው የተሰደዱ ሳይሆኑ ሥርዓቱ በሕዝብ ላይ የሚያደርሰው በደልና ጭቆና፣ችግርና ድህነቱ እነሱንም የጎዳ በመሆኑ ከዚያ ሰው በላ ሥርዓትና ድህነት ለመላቀቅና ለመሸሽ ሲሉ ያልሆኑትን በግድ እንዲቀበሉ ተገደዋል።አሳልፎ የሸጣቸውም ይኸው መንግሥቱና የሚመራው አስተዳደር ነው።አሁን ተቆርቋሪ መስሎ ሲቀርብ የፈጸመው በደል የተዘነጋ ይመስለው ይሆናል።ግን የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ ነውና በፈላሻ ላይ የፈጸመውን ግፍና በደል እንኳንስ የግፍ ጽዋ የቀመሱት ቀርቶ ሌሎቹም አይዘነጉትም። አስታውሱኝ ካለ እሱ እራሱ በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ የሆነውን በጥቂቱ ለማሳየት እወዳለሁ።ፈላሻዎችን ለእስራኤላውያን በመሣሪያና በገንዘብ መሸጡን እንዴት እረሳው?በወቅቱ የራሱ ጓደኛና የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣን የነበረው ፍስሃ ደስታ የተባለው ቀንደኛ የደርግ ወንጀለኛ አውሮፓን በተለይም ሆላንድን በጎበኘበት ወቅት ከደች ፓርላማ አባላት የቀረበለት ዋና ጥያቄ ለምን ፈላሻዎች ወደ እስራኤል እንዲሄዱ አትፈቅዱም? የሚል ጥያቄ ሲሆን የሰጠውም መልስ መንግሥት እየተነጋገረበት ነው፤በቅርቡ መልስ ያገኛል፤የመሄድ መብታቸው ይረጋገጣል የሚል ነበር።ሆላንዶች በዚያን ጊዜ ያሳሰባቸው እንደ ቅጠል ይረግፍ የነበረው የኢትዮጵያ ወጣት ሳይሆን ለእስራኤል ጥቅም የሚሰዋላቸውን እርካሽና ደሃ ሕዝብ በስበብ ባስባቡ መሰብሰቡ ነበር።የፈላሻዎች መውጣት ሌላ ይዞት የሚመጣው ችግር እንዳለ፣ከወደፊቱ ጥቅም ጋር የተያያዘ እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ ሁሉም ልብ እንዲለው አሳስባለሁ። በተወሰዱበት ሰሞን የድርቅ አደጋ አገሪቱን የወጠረበት በመሆኑ በእርዳታ ስም የአሜሪካን ሴኔት አባል የነበረው የሟቹ ፕሬዚደንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ወንድም ቴድ ኬነዲ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ነበር፤የጉብኝቱ ተደራቢ ሥራ የፈላሻዎቹን ከኢትዮጵያ መውጣት ማስተካከልና ማጥናት ነበር።ይህንን በሚመለከት የሙሴ ዘመቻ(Operation moses)የሚለውን መጽሃፍ ማንበቡ ለግንዛቤ ይረዳል።በተረፈም በቅርቡ በጃንዋሪ 6 ቀን 2012 ወያኔ በስልጣን ላይ እንዲወጣ ከጣሩትና ከረዱት የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣኖች አንዱ ኸርማን ኮህን በኢሳት ቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ በሰጡት

ቃለምልልስና ማብራሪያ ደርግ ፈላሾችን በነጻ እንዲወጡ እንዲፈቅድ 35፣ሚሊዮን ብር እንደተከፈለውና ገንዘቡም ኒው ዮርክ በሚገኘው የመንግሥት የባንክ ሂሳብ ቁጥር እንደገባ እንዲህ ሲሉ አጋልጠዋል። Ámbassador cohen also revealed that the us government had also given priority for the air lifting of Ethiopian jews.also known as Felashas.During the last hours of the military junta ,the government of Israel paid $35 million as ransom,which was deposited in the government´s account in New York.

በዚያ ቀውጢና የመከራ ሰዓት በመከረኞቹ ወገኖቻችን ላይ ለመጠቀም ያልሞከረና ያልተሰለፈ አልነበረም፡ከአገር ውስጥ ደርግ፣የኤርትራ ግንባሮችና ፣ወያኔ ከውጭ ደግሞ ሌላው ሳይቀር የእስራኤል ጠላት የሆነችው የሱዳን መንግሥት በጥቅም ተገዝቶ በሚስጥር በመተባበር የአገሩን መሬት ና አየር የመተላለፊያ በር እንዲሆን ለግሷል።

በወገኖቻችን ፍልሰት በማቀነባበሩ ሥራ ላይ የመንግሥቱ ሃ/ማርያም ዘመድና አብሮ አደግ እንዲሁም የኢሰፓ አባል የነበረው አሁን በአሜሪካ አገር የሚኖረውና መንግሥቱ ለጻፈው መጽሃፍ አነሳሽና አቀናባሪ የሆነው ካሣ ከበደ የሚባለውም ወሳኝ ሚና እንደተጫወተ በስፋት ይነገራል።እንደሚባለው ይህ ግለሰብ በእስራኤል አገር ውስጥ ስለተማረ የሂብሩ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ከእስራኤሎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንደነበረው ነው።በመጨረሻውም ወቅት ላይ የደርግ ስርዓት ሊፈራርስ ሲቃረብ በተዘጋጀው የመጨረሻው የፈላሾች ጉዞ የአውሮፕላን በረራ እራሱን ለዋውጦና ተመሳስሎ ወደ እስራኤል እንደሄደ ይነገራል።እንግዲህ ይህ አባባል እውነት ከሆነ ግለሰቡ በሽያጩ ውልና ስምምነት ላይ ሚና ነበረው ማለት ነው።ይህንን በወሬ ደረጃ ከመስማት በቀር ማስረጃ ስለሌለኝ እርግጠኛ ለመሆን አልችልም።ማስረጃ ያላቸው ሰዎች ቢቀርቡና ቢያጋልጡ በወገኖቻችን ላይ ለተፈጸመባቸው በደል በአጠቃላይ በአገራችን ላይ ለደረሰው ውርደት ማገገሚያ ሊይሆን ይችላል።

የዚህን ጉደኛ በመጽሃፍ የሰፈረ ውሸት ለማጋለጥ ሌላ መጽሃፍ ስለሚያስፈልገው በተጨማሪም ደርግ በሥልጣን ላይ ከወጣበት ከስምንት ወራት በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላልነበርኩ የተደረገውን ከመስማት በቀር ባለማየቴ ከጻፈው ጋር ለማመሳከር አልችልም፤ስለሆነም የውሸቱን ጫፍ ጫፉን ነካክቼ ካሳየሁ የአንባቢውን ጊዜ ለመቆጠብ ስል እዚህ ላይ አቆማለሁ።ከኔ የበለጠ በአገር ውስጥ በመሆን እስከመጨረሻው ድረስ የሚያውቁት ሰዎች መጽሃፉን በጥልቀት እየመረመሩ ሕዝቡ በተለይም አዲሱ ትውልድ በደርግና በሌሎቹ ሥርዓቶች ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው የማድረግ ታሪካዊ አላፊነት አለባቸው እላለሁ።ያ ካልሆነ ግን ያገራችን ታሪክ የውሸት መደብል ይሆንና ሲያሳፍረን ይኖራል።ውሸታሞቹም ሳይጋለጡ እንደ ታሪክ ሠሪ እንዲቆጠሩ ያደርጋል። ታሪክ ማለት በእውነት ላይ የተመሠረተ ድርጊት ነው።ታሪክ ማለት ግለሰብ እንደሚፈልገው የሚያቀርበው ልብ ወለድወሬና የፈጠራ ተረት አይደለም።

በሌላው አገር ሕዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙ አምባ ገነኖች ለዓለም አቀፍ  ፍርድ ሲቀርቡ፣ከሥልጣን ሲወገዱ እያየን እኛ እንዳልተበደልን ዝም ብሎ መቀመጡ በታሪክ ያስጠይቀናል፤በግፍ ያለቁትና የሚያልቁትም ወገኖቻችን አጽምና የፈሰሰው ደም ይወቅሰናል።ሌላው ቢቀር ግፈኞች ያለፉትም ሆኑ አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት ወደፊት

በኢትዮጵያ በሚቋቋመው ሕዝባዊ መንግሥት ፍርድ ቤት ለፈጸሙት በደል ፍርዳቸውን እንደሚያገኙ በማሰብ ከአሁኑ መዘጋጀት ይኖርብናል።የሕግ አዋቂዎቹም በመጽሃፉ መሰራጨት ዙሪያ የሚሰነዝሩትን ትችት ጋብ አድርገው ጸሃፊው ለፈጸመው ወንጀል የሚጠየቅበትንና ለፍርድ የሚቀርብበትን መንገድ ቢያጠኑና ቢያስተባብሩ የዜግነት ድርሻቸውንና የሙያ ግዳጃቸውን መወጣት ስለሚሆን ፊታቸውን ወደዚያ እንዲያዞሩ በግፍ በተጨፈጨፉት ኢትዮጵያውያን ስም እጠይቃቸዋለሁ።

በአምባገነኖች ላይ የሚደረገው ዘመቻ ይፋፋም!

ኢትዮጵያን አንድነቷ የተጠበቀ፣ሰብአዊ መብት የተከበረባት፣ፍትህና የዲሞክራሲ ሥርዓት የሰፈነባት አገር ለማድረግ ተባብረን እንነሳ!!

ለዚህ ዓላማ የተሰለፉት ሁሉ የአንድነት ግንባር አቋቁመው መታገል ይኖርባቸዋል።የየግል ድርጅታዊ ዝናና ጥቅምን ጥሎ በተቻለ ፍጥነት ጉባኤ ማካሄድ አስፈላጊና ወቅታዊ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው።ለአንድነት ግንባር ምሥረታ ውይይት የሚተላለፈውን ጥሪ መቀበልና አለመቀበል ማን ለምን ዓላማ እንደቆመ የሚያሳይ መስተዋት ነው። እኔ ካልመራሁት የሚለው የቆዬ በሽታ መወገድ ይኖርበታል።በጋራ የጋራ አመራር መፍጠር ይቻላል።

የምንለውን በተግባር እንተርጉመው!!!

ከሰላምታ ጋር

አገሬ አዲስ